- ኢየሱስ ወደ ምድር የሚመለሰው ሰዎችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ለማዳን ነው?

- አይደለም።

- ለምን?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ቀደም ሲል ሰዎችን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል የማዳን ሥራውን አጠናቅቋል።

- ሊቀ ካህናቱ ኢየሱስን፥ ክርስቶስ እንደ ሆነ ወይም እንዳልሆነ ሲጠይቀው ኢየሱስ የመለሰውን መልስ ታስታውሳላችሁ?

ማርቆስ 14፡61-62

61- ኢየሱስ ግን ዝም አለ፤ ምንም መልስ አልሰጠም። ሊቀ ካህናቱም ኢየሱስ እንደገና፣ የብሩኩ ልጅ፣ ክርስቶስ አንተ ነህን? ሲል ጠየቀው።

62- ኢየሱስም «አዎ ነኝ፤ የሰው ልጅ በኃይሉ ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይ ደመናም ሲመጣ ታዩታላችሁ» አለ።

- ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመለስ እንደ አዳኝ ሳይሆን እንደ ፈራጅ ሆኖ ነው የሚመጣው።

- ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመለስ ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን ባላመኑት ላይ ሊፈርድ ይመጣል።

- ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመለስ በእግዚአብሔር የማያምኑትን ሁሉ ወደ ዘላለማዊ የእሳት ባሕር ይሰድዳቸዋል።



## ትምህርት 68

1. ሰዎች ኢየሱስን ከመስቀላቸው በፊት ምን አደረጉት?

ሀ- ገረፉት አፌዙበትም።

ለ- መቱት ተፉበትም።

ሐ- በራሱም ላይ የእሾኽ አክሊል አደረጉ።

2. የእሾኽ አክሊሉ የምን ምልክት ነበር?

ሀ- የእሾኽ አክሊል የእግዚአብሔር ርግማን ምልክት ነበር።

3. ወታደሮች በኢየሱስ ራስ ላይ የእሾኽ አክሊል ማድረጋቸው የምን ምልክት ነበር?

ሀ- ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ርግማን መሸከሙን የሚያሳይ ምልክት ነበር።

4. በምድር ሁሉ ላይ ለሦስት ሰዓት ያህል ጽቅድቅ ጨለማ የሆነው ለምን ነበር?

ሀ- የሦስቱ ሰዓት ጨለማ ምልክት ነበር።

5. በምድር ሁሉ ላይ የነበረው የሦስት ሰዓት ጨለማ የምን ምልክት ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን በመስቀል ላይ መተውን የሚያሳይ ምልክት ነበር።

6. እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን የተወው ለምን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን የተወው ስለ እናንተ ስለ እኔና ስለ ሰዎች ሁሉ ኃጢአት በመስቀል ላይ እየቀጣው ስለ ነበር ነው።

- ኢየሱስ ለሦስት ቀንና ለሦስት ሌሊት በመቃብር ውስጥ ቆየ።

- በሦስተኛው ቀንና ሌሊት ማብቂያ ማለዳ ላይ ኢየሱስ አዳኝ አምላክ መሆኑን ከሚያምኑት ሴቶች መካከል አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ ሄዱ።

ማርቆስ 16፡1

1- ሰንበት ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም፣ የያዕቆብ እናት ማርያምና ሰሎሜ ሄደው የኢየሱስን ሥጋ ለመቀባት ሽቱ ገዙ።

- እነዚህ ሴቶች ወደ ኢየሱስ መቃብር የሄዱት ለምን ነበር?
- ሴቶቹ የኢየሱስን አስከረን በሽቱ ለመቀባት ፈልገው ነበር።

- በአይሁድ ባሕል አስከረን ከመቀበሩ በፊት ሽቱ መቀባት የተለመደ ነበር።

- ኢየሱስ በችኮላ ስለ ተቀበረ ሴቶቹ የኢየሱስን አስከረን ሽቱ የሚቀቡበት ጊዜ አልነበራቸውም።

- ሴቶቹ ወደ መቃብሩ ሲደርሱ ምን አዩ?

ማርቆስ 16፡2-4

2- በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ጠዋት በማለዳ፣ ገና ፀሓይ እንደ ወጣች፣ ወደ መቃብሩ በመሄድ ላይ ሳሉ፣

3- «ድንጋዩን ከመቃብሩ ደጃፍ ላይ ማን ያንከባልልናል?» በማለት እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር።

4- ቀና ብለው ሲመለከቱ፣ በጣም ትልቅ የነበረው ድንጋይ ከደጃፉ ላይ ተንከባሎ አዩ።

- መቃብሩ የተዘጋበትን ትልቅ ድንጋይ ማን አንከባለለው?



- ከብዙ ዘመናት በፊት እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት በተናገረው መሠረት አዳኙ ወደ ሰማይ ተመለሰ።

የሐዋርያት ሥራ 1፡10

10- እርሱም በሚሄድበት ጊዜ [ደቀ መዛሙርቱ] ትኩር ብለው ወደ ሰማይ ሲመለከቱ፣ እነሆ፣ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ድንገት አጠገባቸው ቆሙ።

- ነጫጭ ልብሶች ለብሰው በደቀ መዛሙርቱ አጠገብ የቆሙት ሁለት ሰዎች እነማን ነበሩ?

- ሁለት የእግዚአብሔር መላእክት ነበሩ።

- መላእክቱ የኢየሱስን ደቀ መዛሙርት ምን አሏቸው?

የሐዋርያት ሥራ 1፡11

11- እንዲህም አሏቸው፤ «እናንተ የገሊላ ሰዎች ሆይ፤ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ እዚህ የቆማችሁት ለምንድን ነው? ይህ ከእናንተ ዘንድ ወደ ሰማይ ሲያርግ ያያችሁት ኢየሱስ፣ ልክ ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት በዚሁ ሁኔታ ይመለሳል።»

- መላእክቱ ኢየሱስ ወደ ምድር ተመልሶ ይመጣል አሉ።

- ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመለስ ምን ያደርጋል?

- አይመልሰውም።
- ለምን አይመልሰውም?

- ምክንያቱም ሰውዬው በእስር ላይ ለአንድ ዓመት በመቆየት ለሠረቀው ላም ቅጣቱን በሙሉ ከፍሏል።

- ኢየሱስ ለሰዎች ኃጢአት የሚገባውን ቅጣት ሙሉ በሙሉ ስለ ከፈለ እግዚአብሔር ከሞት አስነሣው።

- ኢየሱስ ሲሞት እግዚአብሔር የቤተ መቅዱሱን መጋረጃ ለሁለት የከፈለው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር የቤተ መቅደሱን መጋረጃ ለሁለት የከፈለው ከእንግዲህ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ልዩነት እንደማይኖር ለማሳየት ነበር።

- ከእንግዲህ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ልዩነት የማይኖረው በምን ምክንያት ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ከእግዚአብሔር የለየውን የኃጢአት ዋጋ ሙሉ በሙሉ ስልከፈለ።

- ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ሄደው የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች እንዲነግሩ ካዘዛቸው በኋላ ወደ ሰማይ ተመለሰ።

የሐዋርያት ሥራ 1፡9

9- ኢየሱስም ይህን ካለ በኋላ እያዩት ወደ ላይ ዐረገ፤ ደመናም ከዐይናቸው ሰወረችው።



- እግዚአብሔር መልአኩ ልኮ ድንጋዩን አንከባለለው።

- ሴቶቹ ወደ መቃብሩ ገብተው ምን አዩ?

ማርቆስ 16፡5

5- ወደ መቃብሩ እንደ ገቡም፣ ነጭ ልብስ የለበሰ ጐልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ አዩና ደነገጡ።

- ሴቶቹ ወደ መቃብሩ እንደ ገቡ መልአክ አዩ።

- መልአኩ ሴቶቹን ምን አላቸው?

ማርቆስ 16፡6

6- እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ «አትደንግጡ፤ የምትፈልጉት የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ነው፤ እርሱ ተነሥቶአል፣ እዚህ የለም፤ እርሱን ያኖሩበት ስፍራ ይኸውላችሁ።»

- መልአኩ ስለ ኢየሱስ ምን አለ?
- መልአኩ ኢየሱስ በዚያ ያለመኖሩን ተናገረ።

- ኢየሱስ በዚያ ያልነበረው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ኢየሱስ ከሞት ስለተነሣ ነው።

- መልአኩ ኢየሱስ ከሞት እነሣለሁ ብሎ እንደ ተናገረው ከሞት ተነሥቶአል አለ።

- መልአክ ደግሞ ሴቶቹ ፈጥነው ሄደው ኢየሱስ ከሞት መነሣቱን ለደቀ መዛሙርቱ እንዲናገሩ አዘዛቸው።

ማርቆስ 16፡7-8

7- ነገር ግን ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱና ለጴጥሮስ፣ ‘ቀድሞአችሁ ወደ ገሊላ ይሄዳል፣ እንደ ነገራችሁ እዚያ ታገኙ ታላችሁ’ ብላችሁ ንገሯቸው። »

8- ሴቶቹም እየተንቀጠቀጡና እየተደነቁ ከመቃብሩ ሸሽተው ወጡ፤ ፈርተው ስለ ነበር ለማንም አንዳች አልተናገሩም።

- ሴቶቹ በጣም ፈርተው ስለ ነበር በመጀመሪያ ለደቀ መዛሙርቱ አልተናገሩም።

- በኋላ ላይ ከሴቶቹ አንዷ መግደላዊት ማርያም ለደቀ መዛሙርቱ ለመንገር ሄደች።

ማርቆስ 16፡9-13

9- በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ማለዳ ከሙታን ከተነሣ በኋላ፣ ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለማርያም መግደላዊት በመጀመሪያ ታየ።

10- እርሷም ሄዳ፣ ከእርሱ ጋር የነበሩት እያዘኑ ሲያለቅሱ አግኝታ እርሱ ሕያው መሆኑንና ለእርሷም መታየቱን ነገረቻቸው፤

11- እነርሱ ግን፣ ኢየሱስ በሕይወት መኖሩን እና እሷም እንዳየችው በሰሙ ጊዜ አላመኑም።

12- ከዚህ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱ ወደ ገጠር ሲሄዱ በሌላ መልክ ታያቸው።

13- እነርሱም ተመልሰው ይህንኑ ለቀሩት ነገሯቸው፤ ይሁን እንጂ እነርሱንም አላመኗቸውም።



- እግዚአብሔር አብ ለኢየሱስ የሰጠው ሥራ የተጠናቀቀው እንዴት ነው?

- የኢየሱስ ሞት የሰዎችን ሁሉ የኃጢአት ዋጋ ሙሉ በሙሉ ስለከፈለ ነው።

- የኢየሱስ ደም የሰዎችን ሁሉ የኃጢአት ዋጋ ሙሉ በሙሉ ስለከፈለ ነው።

- ኢየሱስ ሰዎችን ለማዳን የሠራው ሥራ መጠናቀቁን እንዴት እናውቃለን?

- የኢየሱስ ሞት ለሰዎች ሁሉ የሚሆን ፍጹም መሥዋዕት በመሆኑ ነው።

- የኢየሱስ ደም ለሰዎች ሁሉ የሚሆን ፍጹም መሥዋዕት ስለሆነ ነው።

- ኢየሱስ ሰዎችን ለማዳን የሠራው ሥራ መጠናቀቁን በሌላ በምን እናውቃለን?

- እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን ከሞት በማስነሣቱ።

- ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ለማዳን የሠራው ሥራ ባይጠናቀቅ ኖሮ እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን ከሙታን አያስነሣውም ነበር።

- እግዚአብሔር በኢየሱስ ፍጹም የኃጢአት ክፍያ ባይረካ ኖሮ እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን ከሞት አያስነሣውም ነበር።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡

- አንድ ሰው ላም ይሠርቅና ለአንድ ዓመት ያህል እሥር ቤት ይቆያል።
- በዓመቱ መጨረሻም ከእስር ይፈታል።

- ፖሊስ ሰውዬውን ከእስር ቤት ውጭ ቢያገኘው ወደ እስር ቤት ይመልሰዋል?

- እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት የተቀበለውና የቃየንን መሥዋዕት የተወው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም አቤል የበግ ጠቦት ደም ሲያቀርብ ቃየን ግን ይህንን ስላላቀረበ ነበር።

- እግዚአብሔር የግብፃውያንን የበኩር ልጆች ገድሎ የእስራኤላውያንን የበኩር ልጆች ያለፈው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እስራኤላውያን የበግ ጠቦት ደም በቤቶቻቸው በር ቀብተው ስለ ነበር ነው።

- ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ ነው።

- እግዚአብሔር አብ ስለ ኃጢአታችን ዋጋ ይሆን ዘንድ ኢየሱስን እንደ በግ ሠዋው።

- ኢየሱስ እኛን ለማዳንና ለኃጢአታችን ዋጋ ለመክፈል ደሙን አፈሰሰ።

- ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት «ተፈጸመ» አለ።
- ኢየሱስ «ተፈጸመ» ሲል ምን ማለቱ ነበር?

- ኢየሱስ ሕይወቱ ማብቃቱን መናገሩ ነበር?
- አይደለም።

- ታዲያ ኢየሱስ በመስቀል ላይ «ተፈጸመ» ሲል ምን ማለቱ ነበር!

- ኢየሱስ ሰዎችን እንዲያድን እግዚአብሔር አብ የሰጠው ሥራ ተጠናቀቀ ማለቱ ነበር።



- መግደላዊት ማርያምና ሌሎች ሁለት ሰዎች የኢየሱስን ከሞት መነሣት ለደቀ መዛሙርቱ ቢነግሯቸውም ደቀ መዛሙርቱ አላመኗቸውም።

- ስለዚህ ኢየሱስ ራሱ ለደቀ መዛሙርቱ ታየ።

ማርቆስ 16፡14

14- ከዚያም አሥራ አንዱ በማዕድ ላይ ሳሉ ተገለጠላቸው፤ ከተነሣ በኋላ ያዩት ሰዎች የነገሯቸውን ስላላመኗቸው፤ አለማመናቸውንና የልባቸውን ድንዳኔ ነቀፈ።

- ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለምን ነቀፋቸው?

- ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ከሙታን መነሣቱን ስላላመኑ።

- ቀጥሎም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ትእዛዝ ሰጣቸው።

ማርቆስ 16፡15

15- ኢየሱስ እንዲህም አላቸው፤ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።»

- ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው ትእዛዝ ምን ነበር?

- ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰብኩ።

- ወንጌል ምንድን ነው?
- የእግዚአብሔር ቃል ነው።

- ኢየሱስ ይህን ትእዛዝ የሰጠው ለደቀ መዛሙርቱ ብቻ ነው?
- አይደለም።

- ኢየሱስ ይህን ትእዛዝ የሰጠው ለደቀ መዛሙርቱና በእርሱ ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ነው።

- ኢየሱስ በእርሱ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ለሌሎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲነግሩ ይፈልጋል።

- ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ስለሚወድ ሰዎችን ሁሉ ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ማዳን ይፈልጋል።

ዮሐንስ 3፡16

16- ኢየሱስ እንዲህ አለ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና።»

- የእግዚአብሔርን ቃል የምንነግራችሁ ለዚህ ነው።

- ሰዎች እንዳይሞቱ፥ ወደ እሳት ባሕርና ወደ ዘላለም ቅጣት እንዳይሄዱ ነው።

- ኢየሱስ የሞተው ለምንድን ነው?

- ኢየሱስ ኃጢአት ሠርቷል?
- አልሠራም።

- ታዲያ ኢየሱስ ለምን ሞተ?



- ሰዎች ሁሉ ኃጢአት ስለ ሠሩ እግዚአብሔር ኃጢአትን ስለሚቀጣና የኃጢአታችንን ቅጣት መክፈል ስላለብን።

- ለኃጢአት የእግዚአብሔር ቅጣት ምንድን ነው?
- ሞት።

- ሰዎች ሁሉ ኃጢአትን ስለ ሠሩ የእግዚአብሔር ቅድስና ኃጢአት በሞት እንዲቀጣ ይጠይቃል።

- ለኃጢአት ከሞት በስተቀር ሌላ ክፍያ የለውም።

- ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ስለሚወደን እንድንሞት አይፈልግም።

- እኛ በሕይወት እያለን ኃጢአታችን በሞት የሚቀጣው እንዴት ነው?

- በእኛ ምትክ አዳኙ አምላክ ኢየሱስ ሞተ።
- እኛ በሕይወት እንድንኖር አዳኙ አምላክ ኢየሱስ ሞተ።

- ደቀ መዛሙርቱ ያልተረዱት ይህን ነበር።

- ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ቢሞትም እንደሚያድናቸው አልተረዱም ነበር።

- ደቀ መዛሙርቱ የኢየሱስ ሞት ብቻ ሊያድናቸው እንደሚችል አልተረዱም ነበር።

- የኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞት ለኃጢአታችን የተከፈለ ዋጋ ነበር።

- በመስቀል ላይ የፈሰሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ለኃጢአታችን የተከፈለ ዋጋ ነው።